**ዓለም አቀፍ የአምሓራ ግብረኃይል (ዓ/አ/አ/ግ/ኃ)**
**International Amhara Task Force (IATF)**

ዓአአግኃ መ/ቁ - 000፪/፳፻፲፰
ጥቅምት ፱/ ፳፻፩፰ ዓ/ም

# ከዓለም አቀፍ የአማራ ግብረኃይል የተሰጠ ወቅታዊ መግለጫ

## የአረመኔው የአብይ አህመድ ፋሽስት ሰራዊት በወጣት አርበኛ ሴቶቻችን ላይ የፈጸመውን የጭካኔ ጥግ መላው ዓለም ሊያውቀውና ሊያወግዘው ይገባል!!!









| ፋኒት በዓለም ዋሴ | ፋኒት ትግስት ወዳጅ ይመር | ፋኒት መቅደስ ተስፋዬ |
|---|---|---|

የፋኖ ሰራዊት የጠላት ወታደር ቁስለኛ ምርኮኛ በቅድሚያ ህክምና እንዲያገኝ ሲያደርጉ፣ ሌላውም ምርኮኛ ደግሞ በምህረት ወደ ቤተሰቦቹ እንዲሄዱ ያደርጋሉ። ምርኮኞች ቁጥራቸው በርከት ሲልም ዓለም አቀፍ ቀይ መስቀልን በመጠየቅ እንዲረከባቸው ያደርጋሉ። የታወቀውን የዓለም አቀፍ ምርኮኛ አያያዝን ህግ ያከብራሉ። ይህ በፋኖ ዘንድ የተለመደ አሰራር ነው።

የ 19 ዓመትዋ ወጣቷ በዓለም ዋሴ እንደማንኛውም ወጣት የራሷን ኑሮ አመቻችታ እንደ ከሌላው ወጣት ጋር ተመሳስላ መኖር ትችል ነበር፤ ሆኖም ግን በአማራው ሕዝብ ላይ የሚደርሰው ሰቃይና መከራ፣ ሰደትና መፈናቀል፣ መገደልና መጨፍጨፍ አንገብግቧት ይህን አረመኔ የአብይ አህመድ ፋሽስት አገዛዝን ለመፋለምና ነጻነቷን ለማስከበር ቆርጣ ወስና የህልውና ትግል ከሚያደርገው ፋኖ ጋር በአርበኝነት ተቀላቀለች። በፋኖም ውስጥ የመደበኛና የኮማንዶ ስልጠናዎችን ጨርሳ የአፋብኃ ቲዎድሮስ እዝ 5ኛ ክፍለ ጦር አባል ሆና ከሌሎች ጓዶቿ ጋር ለቅኝት ሰራ ተሰማርታ እያለ ድንገት በአረመኔው የአብይ አገዛዝ ወታደሮች ቀለበት ውስጥ ወደቀች። ጥቂት አርበኞች ሆነው የሚችሉትን ያህል ቢዋጉም የአብይ አህመድ ወታደሮች በርካታ ነበሩና ጥቅምት 2 ቀን 2018 በጥይት ቆስላ ተማረከች።

በአረመኔው አብይ አህመድ አገዛዝ ወታደሮች ግን በጥላቻና በተነገራቸው የሃሰት ትርክት ነው የሚመሩትና ይህች የ 19 ዓመት ወጣት ፋኒት በዓለም ዋሴ ቆስላ ስትማረክ የፈጸሙባት ተግባር ግን ተሰምቶና ታይቶ የማያውቅ አስቃቂ የጭካኔ ጥግ ነው። ቁስለኛዋን ምርኮኛ ልብሷን አወላልቀው “አማራ” የሚለውን እጇ ላይ የተነቀሰችውን ንቅሳት በጩቤ ገፈው፤ ሁለቱንም ጡቶቿን በሳንጃ ቆራርጠው፣ መላ ሰውነቷን በሳንጃ ስለት ወጋግተው በኢስብዓዊነትና እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ

ዓለም አቀፍ የአምሓራ ግብረኃይል (ዓ/አ/አ/ግ/ኃ)
www.internationalamharataskforce.org
iatf@amharataskforce.org

International Amhara Task Force (IATF)
114 Hazellville Road, London
N19 3NA, United Kingdom

አስከሬኗን ማንኩሳ ከተማ መሀል አስፋልት ላይ ጥለው የአረመኔነታቸውን ጥግ ለሕዝብ አሳይተዋል። ይህ ነው የአብይ አህመድ ሰራዊት መለያ!

ከዚያ በፊት መስከረም 30 ቀን 208 ዓ/ም በወገራ የበላይ ዘለቀ እዝ 3ኛ ኮር አምባራስ ክፍለ ጦር አባል የሆነችው አርበኛ ፋኒት መቅደስ ተስፋዬን በመግደል ሬሳዋን በመኪና በመጎተት አስፋልት ላይ ጥለው እንዳትቀበርም አስከሬኗን በጸሀይና በዝናብ እንዲበላሽ በማድረግ ዘግናኝ ድርጊት በመፈጸም የአብይ ሰራዊት የተካነበትን የኢሰብዓዊ ባሕሪውን ለሕዝብ አሳይቷል።

ጥቅምት 7 ቀን 2018 ዓ/ም ደግሞ በራያ በጮቢ በር ግንባር ተጋድሎ እያደረገች የተሰዋችው የምሥራቅ አማራ ኮር አንድ አውጃሮ ክፍለጦር 3ኛ ሻለቃ አባል የሆነችው አርበኛ ፋኒት ትግሥት ወዳጅ ይመር ካስከሬኗ ላይ አንደኛውን ጡቷን ቆርጦ እርቃኗን ሜዳ ላይ ጥሎ ሰቅጣጭና አረመኔያው ድርጊት የፈጸመው በጥላቻ የተሞላው የአብይ አህመድ ሰራዊት ነው።

አማራ ሆኖ በአማራው ላይ ይህንን የመሰለ የጭካኔ ተግባር ተፈጽሞ እያየንና እየሰማን ልባችንን አደንድነን መቀመጥ አለብን ወይ? ብለን መጠየቅና የህልውና ትግሉን በውስጥም በውጭም ያለን ሁሉ መርዳት ካልቻልን በእያንዳንዳችን ቤተሰብ ላይ ተመሳሳይ ድርጊት ሊፈጸም እንደሚችል መገንዘብና ሁላችንም በጭንቀትና በተሰፋ መቁረጥ ከምንቀመጥ በምንችለው አቅምና መንገድ በተግባር የህልውና ትግሉን መደገፍና መርዳት ይኖርብናል። ይህን አስከፊ የጭካኔ ወንጀልንም መላው ዓለም እንዲያወቀውና እንዲያወግዘው ለተለያዩ የዜና አውታሮች ማድረስ፣ ለዓለም አቀፍ ሰብዓዊ ሙብት ድርጅቶች፣ ለመንግስታት፣ ለኮንግረስና ለፓርላማ አባላት በዘመቻ መልክ ማሳወቅ ይኖርብናል።

በወጣት የሴት አርበኞቻችን ፋኒት በዓለም ዋሴ፣ ፋኒት መቅደስ ተስፋዬና ፋኒት ትእግሥት ወዳጅ ይመር ላይ የደረሰው አስቃቂ አረመኔያዊ ተግባር የፈጸሙት ወንጀለኞችም በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ሰራ መስራት ይኖርበታል። በጀግንነት የተሰዉትን የነፋኒት በዓለም ዋሴንና ጓዶቿ ምስልና ታሪክ በሁላችንም ልብ ተቀርጾ እንዲቀመጥ በየአገሩ ያለን ሁሉ የተለያዩ የፈጠራ ሰራዎች በመስራት ለምሳሌ ምስሎቻቸው ያለበትን ቲሸርት በመልበስ፣ የሻማ ምሽቶች በማዘጋጀት በስማቸው ዝግጅት በማዘጋጀትና የመሳሰሉትን ቢያንስ ማከናወን ይኖርብናል።

የዚህ ፋሽስት ሰራዊት መሪ የሆነው የአብይ አህመድ አገዛዝን ዘመን እንዲያበቃ የማያቆም ዘመቻ መካሄድ ይኖርበታል። በአገርም ሆነ በውጭው ዓለም የሕዝብን ትኩረት ወደ ሌላ አቅጣጫ በማስቀየር የዘረኛውና አረመኔው አብይ አህመድ አገዛዝን እድሜ ለማስቀጠል ፕሮፓጋንዳ በመስራት የሚዳከሩ የሚዲያ ክፍሎች፣ የኢንቨስትመንት ደላላዎች፣ አገር ለአረብ እየተሸጠች "አዲስ አበባ አሸበረቀች አማረች" እያሉ ከንቱ ስብከታቸውን የሚያሰሙና በውስጥም በውጭም ሕዝብን ማዘናጊያ በርካታ የመዝናኛ እና የተለያዩ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ሀገር ሰላም የሆነች ይመስል ሕዝብን ዳንኪራ የሚያስረግጡና ገንዘቡን በአልባሌና ጭፈራ እንዲያባክን ሰራ የሚሰሩ ግለሰቦችም ሆኑ ተላላኪዎች እንዲሁም ማንኛውም ሰው ከዚህ የሆዳምና የባንዳ ሰራቸው እንዲታቀቡ እንነግራለን። እንመክራለን። ሀብት ለመሰብሰብ በመሯሯጥና የጨለማና የሀዘን ዘመንን በጭፈራና በደስታ ለማሳለፍ የሚዳከሩትን ሁሉ እግዚአበሔር ልቦና ይስጣችሁ፣ ነገ ይህች አገር ስትጠፋ ተመልሳችሁ አገር አልባና ጨለማ ውስጥ የምትወድቁ መሆናችሁን እንድታወቁት፤ በታሪክም በሕዝብም ተወቃሽና ተጠያቂ መሆናችሁንም አትዘንጉ እንላለን!

የነፋኒት በዓለም ዋሴ ጀግንነት አርዓያ ሊሆነን፣ የተፈጸመባቸው አስቃቂ ድርጊትና እንዲዘገንነን እንዲቆጠቁጠን ነግ ተነግወዲያ በሌሎችም ጀግና እህቶችና ወንድሞቻችን ላይም  እንዳይደገም ማድረግ የሁላችንም የህሊና ግዴታ ነውና በየከተማው በተለያዩ ምክንያቶች ተዳክመን፣ ፈዘንና ደንዝዘን በተለያዩ ምክንያቶች ተስፋ ቆርጠን የቆየን ሁሉ፤ የባሰ እየመጣ ነውና ወጣት አርበኞቻችንን ወገኖቻችንን ተጋድሎ ስቃይና ግፍን በማስታወስ እንደገና እንነሳ! እንበረታታ! እግዚአብሄር ለተሰዉት አርበኞቻችን ቤተሰቦችና ጓዶች መጽናናቱን ይስጥልን። ፈጣሪ ነፍሳቸውን በገነት ያኑርልን። እግዚአብሔር የአማራውን የህልውና ትግል ይባርክ!

ድል ለአማራ የህልውና ትግል! የአማራው ህልውና የኢትዮጵያም ህልውና ነው!!!
የአረመኔውአብይ አህመድ አገዛዝ ያብቃ! ወንጀለኞችም ለፍርድ ይቅረቡ!!!

**ዓለም አቀፍ የአምራ ግብረኃይል (ዓ/አ/አ/ግ/ኃ)**

ዓለም አቀፍ  የአምሓራ ግብረኃይል (ዓ/አ/አ/ግ/ኃ)
www.internationalamharataskforce.org
iatf@amharataskforce.org
International Amhara Task Force (IATF)
114 Hazellville Road, London
N19 3NA, United Kingdom